የረቡዕ ጥር 4 1997 ዓም( ጃንዋሪ 12 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ዐባይ ጠፍቶ እንዳያስጠፋን

ለአለፉት ሠላሳ ዓመታት የግብፅ የሳይንስ ጠቢባን በሀገራቸውና በውጭ ሀገሮች የኑክሌር ምርምርና ሙከራ ሲያካሂዱ እንደቆዩ፥ ዘ ዋሽንግተን ፖስት የተሰኘው የአሜሪካ ጋዜጣ በቅርቡ በጃንዋሪ 5 ቀን 2005 ዓም ባወጣው ዕትሙ አስፍሮታል። የዓለምአቀፍ አውቶሚክ ኃይል ድርጅት በበኩሉ፥ በግብፅ መንግሥት ቁጥጥር ስር የሚገኘው የኑክሌር ምርምርና ጥናት ተቋም፥ እስከ አሁን ድረስ ምን ውጤት እንዳስመዘገበ አይታወቅም ብሏል። ግብፅ፥ የአውቶሚክ መሳሪያን ለመስራት የቱን ያህል ርምጃ እንደተራመደች ባይታወቅም፥እስከ አሁን ድረስ ግን፥ ኒኩላርን ለመስራት የሚያስችሉ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን፤ ማለትም፥ ዩራኒየምና ፐሉቶኒየም የተሰኙትን ንጥረ ነገሮችን አዳብራ ለማከማቸት ምን ያህል ችሎታ እንዳላት በትክክል የሚናገር የለም። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሳይንትፊክ ጆርናል በተሰኘው መጽሂታቸው፥ የግብፅ የኒኩሌር ሳይንቲስቶች ባወጡት ዜና ለማወቅ እንደተቻለው፥ የግብፅ የኑክሌር ኃይል ምርምርና ሙከራ፥ በግብፅ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንዳልሆነ ለመሸፈን ጥረዋል። የዓለም አቀፍ የኑክሌር ኃይል ድርጅት ቃል አቀባይ ም/ር ማርክ ግዋዝዲክ በበኩላቸው፥ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል።

የኒኩሌር ጦር መሳሪያን ለመገንባት ይጠቅማል የሚባለው ዩሬንየም ኮምፓውንድን ሙከራ ግብፅ፥ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር፥ ከ1970 እስከ 1980 በነበሩት ዓመታት እንዳደረገች ግን ተረጋግጧል። ግብፆች፥ እነኝህን ሙከራዎች ያደረጉት በፈረንሳይና በቱርክ እንደሆነ የሚጠቁሙ ዜናዎች አሉ። ይህንን ዜና አስመልክቶ፥ የዋይት ሐውስና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቃለ አቀባዮች ፥ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ተናግረዋል። ግብፅ፥ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር፥ በ1982 ዓም የኒኩሌር መሳሪያ መጠቀም የሚያግደውን ስምምነት የፈረመች ሀገር ብትሆንም፤የኑክሌር ሳይንስ ጠበብቶቿ ግን በኒኩሌር ሥራ የተሰማሩና ሙከራውንም እያደረጉ መሆናቸው ተደርሶበታል። ይህ ዜና ደግሞ፥ የኑክሌር መሳሪያ መስራትን የሚከለክለውን ስምምነት ከመፈረሟ ጋር የሚፃረር ሆኗል በማለት ተመልካቾች ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ግብፅ እስካሁን የኒኩሌር ምርመራን አስመልክታ ምን ያህል ጉዞ ለመሄድ እንደቻለች የሚመረምረው መርማሪ ቡድን፥የሥራውን ውጤት በሚቀጥሉት የየካቲትና መጋቢት ወሮች ይፋ እንደሚያደርግ ይጠበቃል።ለጉዳዩ ቅርበት ያለቸው የዓለም የኒኩሌር ሳይንስ ጠቢባንና ዲፕሎማቶች፥ እንደሚናገሩት፥ የግብፅ የኑክላር ፕሮግራም ደረጃ፥ ከኢራን፥ ከሰሜን ኮርያ፥ ከሊቢያ ወይም ከደቡብ ኮሪያ ጋር የሚስተካከል አይሆንም ይላሉ። መሥሪያ ቤቱን በኦስትርያ ዋና ከተማ በቪዬና ያደረገው፥ የዓለም

አቀፍ የአዎቶሚክ ኃይል ድርጅት ድሬክተር የሆኑት፥ግብፃዊው ሞሃመድ ኤልባራዲ ይህ ዜና ሊያሳስባቸው እንደሚችል፥አንዳንድ ታዛቢዎች ቢጠቁሙም፥ በኢራክ ጉዳይ ከአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጋር ባለቸው ቅራኔ የተነሳ፥ ለሦስተኛ ጊዜ እንዳይመረጡ አሜሪካ ሙከራ ተዳርጋለች ተብሎ ይታመናል።

ግብፅ የኑክሌር መሳሪያ ባለቤት ለመሆን የምታደረገው ጥረት ዜና፥ ከማነኛቸውም ሀገሮች በላይ ሊያሳስባት የሚችለው ፥ ሀገራችን እንደሚሆን አርቆ አስተዋይ ለሆነው ዜጋ ሁሉ የሚሳነው አይሆንም። ምናልባት ግብፅ የዚህ መሳሪያ ባለቤት የምትሆንበት ጊዜ በርካታ ዓመታትን የሚፈጅ ሊሆን ይችል ይሆን ይሆናል። ያም ቢሆን ግን ኢትዮጵያ የግብፅን የኒኩሌር ፕሮግራም ሂደት በአርምሞ ልታየው የሚገባት ሊሆን አይችልም። እንዲያው ይህን አረፍተ ነገር ለማለት የተገደድነው፥ ለእግር መንገዳችን መግቢያ፥ እንዲሆነን ብለን እንጅ፥አጣዳፊና አንገብጋቢ ትኩረታችን ሊሆን የሚችለው ግን ሌላ ዓቢይ ጉዳይ አለን። እኛ ኢትዮጵያውያን ስለ ኑክሌር ኃይልም ይሁን መሳሪያ አጠቃቀም ከማለማችን ወይም ከመጨነቃችን በፊት፥ ሌሎች የሚያሳስቡንና እንቅልፍ የማያስወስዱ ብርቱ ጉዳዮች አሉን። ሀገራችን ቀስ በቀስ እየጠፋች ወደ ከርስ መቃብሯ ከመግባቷ አስቀድሞ ማዳን ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን። ይህ ዕምነት የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት መሆኑ፥ ማንም ሊጠራጠር አይቻለውም። የሀገርን መኖር የሚተካው አንዳችም ጉዳይ ሊኖር ስለማይችል፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት የሚያስፈልግ አይሆንም።

እረ ለመሆኑ የዛሬ ስድሳ አመት ግብፅና ኢትዮጵያ በምን ደረጃ ላይ ነበሩ? ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፍፃሜ ማግስት፥ ሁለቱም የነበሩበት ሁለንተናዊ ሁኔታ ከሞላ ጎደል የተራራቀ ነበር ማለት አይቻልም። በተለይም በመንግሥት አስተዳደርና ከባዕዳን ተጽዕኖ አኳያ በተመሳሳይ ደረጃ ነበሩ ቢባል ፥ ከዕውነት የራቀ አይሆንም። የልዩነታቸው ዕምርታ በጉልህ ሊከሰት የችአለው፥ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1952 ዓም ፤ ግብፅ በሀገር ወዳድ የጦር መኮንኖቿ አማካኝነት የፋሩቅን ዙፋናዊ መንግሥት አስወግዳ የሪፑብሊክ መንግሥት ከመሠረተችና የእንግሊዝ የእጅ አዙር አገዛዝ ከሀገሯ ካባረረች በኋላ ነበር። ሥልጣን የጨበጡት የጦር መኮንኖቿም ሀገር ወዳድነታቸው እጅግ የላቀ ስለነበር፥ ትኩረታቸው በሃገራቸው ዘላቂ ጥቅምና በሕዝባቸው የኑሮ ደረጃ ዕድገት ላይ ነበር። በመሆኑም ከሁሉ አስቀድመው ዓባይን መገደብ ነበረባቸውና ታላቁን የአስዋንን ግድብ ገድበው፥የዐባይን ውሀ በሚገባ መጠቀም ቻሉ። ሕዝባቸውንም ከረሀብ ከቸነፈር አድነው፥ ጥሩ ተመጋቢ አድርገውታል። ለአምሳ ዓመታት የተፈራረቁት ሦስት መንግሥታት አንዱ በሰራው ላይ መገንባት እንጅ፥ አንዱ የገነባውን ሌላው የሚያፈርስው አልነበረም። በመሆኑም፥ የዛሬ ስድሳ ዓመታት ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ሁኔታ የነበሩት ኢትዮጵያና ግብፅ፥ ዛሬ ያለቡት ሁለንተናዊ ደረጃ ሲታይ፥ የሰማይና የምድር ያህል ተራርቆ ይገኛል። ለዚህም እንደ ትልቅ ማስረጃ የሚጠቀሰው፥ ከላይ እንደተዘረዘረው፥ ግብፅ ዛሬ ከኒኩሌር ዘመን ስትገባ፥ ኢትዮጵያ ግን

ሕዝቧን መመገብ እንኳን አቅቷታል፡፡ ይህ ደግሞ ከላይ ከሰማይ የመጣ ትዕዛዝ ወይም መርገም፥ ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ፥ ግብፆች ከኢትዮጵያውያን የበለጠ ጭንቅላት ኖሯቸው ሳይሆን፤መሪዎቹ ምንም እንኳን ዴሞክራሲያዊ ባይሆኑም የሀገራቸውን ዘላቂ ጥቅም ያስቀደሙ በመሆናቸው ነው፡፡ ከእኛዎቹ ከሀዲዎች ሲነፃፃሩ ማለት ነው፡፡

ወደኛው ሀገር ስናተኩር ሁኔታው የተለየ ነበር፡፡ አሁንም ያው ነው፡፡ እንደ ግብፆቹ ሁሉ፥ እኛም በአለፉት ስድሳ ዓመታት፥ ሦስት መንግሥታት ቢቀያየሩብንም፥ ቢለዋወጡም፥ የሀገራችን ሁኔታ በመሠረታዊ መልኩ ምንም ለውጥ አላገኘም፡፡ ዕርግጥ ግብፅ ለሠላሳ ዓመታት በጦርነት ላይ ብትቆይም፥ እኛም ለአለፉት አርባ ሰባት ዓመቶች በጦርነት ላይ ነበርን፡፡ አሁንም ከጦርነት አባዜ ልንላቀቅ አልቻልንም፡፡ ፍጅቱ፥ አለመረጋጋቱ፥ ለልማትና ለዕድገት የሚያመች ሁኔታ አለመኖሩ፥ ጭቆናው፥ ስደቱ፥ ረሀቡ፥ ድኅነቱ፤ በሽታውና መከራው አሁንም የሕዝባችን የተለመደ ህይወት መሆኑን ቀጥሏል፡፡ የእነኝህ ሁሉ መሠረታዊ ችግሮችና መንስዔዎች፥ ያው ዞሮዞሮ ፀረ ሕዝብና ፀረ ሀገር አምባገነኖች ናቸው፡፡ ይህ ዕውነታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በሚገባ የታወቀ ቢሆንም፥ መፍትሄ ለማግኘት ገና አልተቻለም፡፡ ዘለዓለም፤ ዋይታና ለቅሶ ከማዥጎድጎድ አልፎ ተርፎ፥ ብሔራዊ ችግሮቻችን ለአንዴና ለሁል ጊዜው የምናስወግድበት፥ ዘለቄታ መፍትሄ ማግኘት ተስኖናል፡፡ ለማነኛውም ሀገር ምንነትና ማንነት ዋስትና፥ የሀገሩ ሕዝብ መሆኑ ባያከራክርም፥ ያ ሕዝብ የሚኖረው መንግሥት፥ ግን በማነኛውም መስፈርት ቢመዘን፥ ለሁሉም ነገር፥ ማለት ለጥፋቱም ይሁን ለልማቱ፥ ለሰላሙም ይሁን ሠላም ለማጣቱ፥ ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታል፡፡ በኃላፊነትም ይጠየቃል፡፡ ሀገር ወዳድ መሪ ነው ተብሎ ለመጠራት ቢሞክርም፥የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስካልተመሠረተ ድረስ፥ ሀገር ይለማል፥ ሕዝብ ይበለጽጋል፥ ሠላም ይሰፍናል፤ ዕድገት ይገኛል፤ ወንዞች ይገደባሉ፥ መሠረተ ልማቶች ይስፋፋሉ፥ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ ምጥቀት ይመጣል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ስለ፥ታላቁ አባይ፥ ስለ ታሪካዊው አባይ፥ የዓለም ታሪክ መመዝገብ ከጀመረ አንስቶ፥ ብዙ፥ እጅግ ብዙ ተጽፎለታል ተቀኝቶለታል፥ ተገጥሞለታል፡፡ አያሌ ታሪክም ተመዝግቦለታል፡፡ ከታለቁ መጽሐፍ እስከ ዘመናዊ የፖሊቲካ ትንታኔ ተሰብኮበታል፡፡ ተሰብኮለታል፡፡ በአንድ አካባቢም ተመልኮበታል፡፡ በዘመናት፥ ኮከብ ቆጣሪዎች፤ የውሃ ጠበብቶች( (ሀይድሮሎጅስቶች) ሀገር አሳሾች( ኤክስፐሎረርስ) የጆግራፊ ጠበብቶች ተመራምረውበታል፥ ደራሲያንና ባለቅኔዎች ተቀኝተውበታል፡፡ አባይ ሞኙ ሆይ ብለውታል፤እነ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ገሞራውም ምነዋ ብለው በፍቅር ረግመውታል፡፡ ግብፆችም በሚገባ ተጠቅመውበታል፡፡ ሕይወታቸው በአባይ መኖር አለመኖር መሆኑን በሚገባ ስለተረዱም፥ አባይ ወይም ሞት የሚለው መርኀ፥ የኑሯቸው፥ የዕድገታቸው፥ የኢኮኖሚያቸው፥ የደህንነታቸው፥ የውስጥና የውጭ ፖሊሳቸው መሠረት ነው፡፡ አባይ፥ ለግብፅ ሕይወት አልፋና ኦሚጋ መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ፡፡ ዕውነትም ዓባይ ለግብፆች ህይወት አልፋና ኦሜጋ ነው፡፡ ወደፊት የአባይ አካባቢ ሀገሮች ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥርና

የውሃው መጠን እየቀነሰ ሲመጣ፥ በአካባቢው፥ ሊያስከትል የሚችለውን፥ የፖሊቲካ ለውጥና ችግር፥ በሚገባ አጤነው፥ ዛሬ የግብፅ መሬዎች የኒኩሌር ኃይል ባለቤቶች ሊሆኑ የሚያበቃቸውን ዝግጅትና ጥናት ማድረጋቸው አያስደንቅም:: ወደፊት የኑክሌር መሳሪያቸውን ይጠቀሙበት አይጠቀሙበት ሌላ ጥያቄ ነው:: ግን የኒኩሌር ኃይል ባለቤቶች ለመሆን መወሰናቸው፥ ሌላው ቢቀር እኛ ኢትዮጵያውያ ልንጠራጠር የሚገባን አይመስለንም:: ሊያስገርመንም አይችልም:: ዘለአለም ሊያስገርመን የሚችለው ግን የእኛው የራሳችን ሁኔታ ብቻ ነው:: አሁንም ገና ስለራሳችን፥ ስለሀገራችንና ስለወደፊቱ ዕድላችን ማሰብና መብተክተክ አለመጀመራችን፤ ከራሳችን አልፎ ተርፎ፥ ዓለምን ማስገረሙ ሰነባብቷል:: የሀገሩን ሕዝብ መመገብን አስመልክቶ፥ በውጭ ርዳታና ምፅዋዕት ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ የሚያራምድ ከወያኔ በስተቀር በዓለም ውስጥ ማንም መንግሥት ዛሬ የለም:: ዓባይን ተጠቅመን ከድኅነት መውጣታችን ቀርቶ፥ ወደፊት ዓባይ ጠፍቶ እኛንም እንደሚያሰጠፋን ማሰብ መጀመር አለብን:: የውጭ ጠላቶች ሊያጠፉት እየተዘጋጁ፥ እርስ በዕርሱ የሚጠፋፋ ሕዝብ ማለት አትዮጵያውያን ናቸው ከመባል መዳን ይኖርብናል:: ይህን ከማሰባችን አስቀድሞ ግን፥ ለዚህ ተግባር የሚያበቃንን ቅድመ-ዝግጅት ማድረግ አለብን:: ለዝግጅታችን ሁሉ መሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተን ሀገር ወዳድ፥ ሕዝብ አፍቃሪና ለህግ ተገዥዎች የሚሆኑ መሪዎችን መምረጥ ነው:: ያ ሳይሆን ቀርቶ፥ “ አባይም ቢሞላ፥ ቢሞላ፥ መሻገሪያው ሌላ” እያልን እራሳችንን ብንደልል፥ አባይ ራሱ ጠፍቶ እኛንም ከማስጠፋት አያድነንም:: አባይን አድነን፥ እራሳችንንም ለማዳን ከፈለግን፥ የዛሬዎቹን ፀረ ሕዝብ-ፀረ ሀገር መሪዎች ለመጣል ተባብረን ከመስራት የተሻለ አማራጭና አንገብጋቢ ብሔራዊ አጀንዳ ሊኖረን አይገኝም:: “አባይ ይገደባል፥ ሕዝቡም ይመገባል” ከሚለው የቀቢፀ-ተስፋ መፈክር ወጥተን፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት መታገል የውቅቱ ተግባራችን መሆኑን ለአንድ አፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም:: የግብፅ መንግስታት የአባይን ጥቅም ሰላወቁ ሶማሊያን፤ሱዳንን፤ተገንጣይ ኃይሎችን ሁሉ እያገዙና እየረዱ ኢትዮጵያ ሰላም እንድታጣ ፤ እንድታደከም ሲያደርጉ ቆይተዋል::ዛሬም በዚሁ መንፈስ ቀጥለዋል:: ግብፅ የወያኔ ደጋፊ እንደነበረችም መዘንጋት አንችልም:: ወያኔም ውለታ ከፋይ ሆኖ እነሆ ኢትዮጵያን እያዳከመና እየበታተነ--ማለትም ለግብፅ እያገለገለ ነው:: አባይን ለሀገር ልማት ለማዋል በቅድሚያ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ማስወገድ ይኖርብናል::